# በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ የሚካሄድ ብሄራዊ ምክክር የማስጀመሪያ መርሀ-ግብር መድረክ

## መክፈቻ ንግግር

- የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ - የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣
- የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር - የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣
- የተከበሩ አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣
- የተከበራችሁ የክልል መስተዳድር አፈ-ጉባኤዎች፣ ፕሬዚደንቶች፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች፣ የፍትህ ቢሮ ሃላፊዎች፣ ፖሊስ ኮሚሽነሮች፣
- ክቡራን ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች እና ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣
- ክቡራን አምባሳደሮች እና የአለማቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች፣
- የተከበራቹህ ተጋባዥ እንግዶች፣
- ክቡራትና ክቡራን፣

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ሰፋፊ ግጭቶች መከሰታቸው ይታወቃል። በነዚህ ግጭቶች ምክንያትም ክቡር በሆነው የሰው ህይወት፣ አካል እና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲደርስ ቆይቷል። በቅርብ አመታት - መሰል ግጭቶች እና የእርስ በርስ ጦርነቶች በመቀጠላቸውም ለበርካታ ዜጎች ሞት፣ መፈናቀል፣ ስደት እና ለንብረት ውድመት መንስኤ ሆኗል።

የመንግስት ቀዳሚ ሃላፊነት የህዝብን ሰላም እና ፀጥታ መጠበቅ እንዲሁም የግለሰቦችን ሰብዓዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር ቢሆንም - በቀደመው እና በቀጠለው ውስብስብ የአገራችን የመንግስታት ስርዓት ሒደት - ሰፋፊ እና ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙ ቆይተዋል። በዚህም ምክንያት - በጊዜ ሂደት የበዳይ-ተበዳይ ትርክቶች የተበራከቱበትን እና ቅራኔዎች እጅጉን እንደረጁ የመጡበትን አሳሳቢ ሁኔታ አይተናል።

በሌላ በኩል - እነዚህ ፈታኝ የተደራረቡ በደሎች፣ የመብት ጥሰቶች፣ እና የተዛነፉ የታሪክ አረዳዶች ቢንሰራፉም - እንደአገር በመንግስታዊ ስርአቶቻችን አማካይነት ለጥሰቶቹ የተሰጡ ትኩረቶች እና ምላሾች ምሉዕ ነበሩ ለማለት አይቻልም። በየዘመኑ በዜጎች ላይ የተፈፀሙ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ግሰቶች ተገቢ ፍትህ እንዲያገኙ ባለመደረጉ፣ ተጎጂዎችም አግባብነት ባለው መንገድ አለመካሳቸው፣ እና ሁሉን-አቀፍ ሀገራዊ እርቀ ባለመከናወኑ ምክንያትም - ውስንነቶቻችን ዘርፈ-ብዙ ቁርሾዎች እንዲዳብሩ ከማስቻላቸውም በላይ - አሁን ላይም ቢሆን ለአዳዲስ ግጭቶች ምክንያት እየሆኑ መቀጠላቸው ይታወቃል።

ስለሆነም ሲፈፀሙ ለቆዩ ጥቃቶች፣ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና በደሎች - እውነትን በማውጣት እና ተገቢ ፍትህ በመስጠት - የኖሩ እና የቀጠሉ ማህበራዊ ቁርሾዎችን ማስወገድ፣ እንዲሁም እውነትን መሰረት ያደረገ ሁሉን-አቀፍ ማህበራዊ እርቅን ማስፈን - በሀገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት፣ ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩበት ስርአት ለመገንባት፣ እና ጠንካራ የሀገረ-መንግስት ግንባታ እውን ለማድረግ ፍፁም ቅድመ-ሁኔታ

የሆኑበት የታሪክ ሂደት ላይ ደርሰናል። ከዚህ አንጻር እንደአገር እና እንደ-ማህበረሰብ ራሳችንን በጥልቅ ጽሞና ውስጥ አስገብተንን ማሰላልሰል እና በቀጣይ የምንወስዳቸውን እርምጃዎች በጥንቃቄ እና በማስተዋል መለየት ፍፁም አስፈላጊ ይሆናል።

በዚህ ረገድ - ከራሳቸን የነባራዊ ሁኔታ እይታ ባለፈ - በሌሎች በሽግግር ላይ ባሉ ወይም ከግጭት እና ከባድ የሙብት ጥሰቶች አዙሪት በመውጣት ላይ በሚገኙ ማህበረሰቦች እና አገራት ልምድ እንደታየው - ለቀደሙ እና ስር ለሰደዱ የሰብዓዊ ሙብት ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ በመስጠት ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት - የሽግግር ፍትህ አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ አይነተኛ አማራጭ መሆኑ ተረድተናል።

**ክቡራን እና ክቡራት**

ዛሬ ላይ - በሀገራችን ኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን እውን በማድረግ - ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለህግ የበላይነት መረጋገጥ መሰረት መጣል - ከመቸውም ጊዜ በላይ አስፈላጊነቱ ጎልቶ ወጥቷል። በቀጣይም - የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን በማደራጀት - በአገራችን ግጭቶች እና ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ግሰቶች እንዳይደገሙ ማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ማስፈን የሁላችንም የጋራ ሃላፊነት ይሆናል።

ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ሂደትን ለመጀመር እንደአገር እና እንደ ማህበረሰብ ለወጠንነው ሀሳብ መሳካት ሁሉም የየራሱን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ጥሪዬን እያቀረብኩ - ይህ በብሔራዊ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ የሚካሄደውን የግብዐት ማሰባሰብ እና የምክክር መድረክ በዛሬው እለት በይፋ መከፈቱን አበስራለሁ።

**አመሰግናለሁ!!!**